ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

Solidarity Movement for a New Ethiopia

# ታላቅ ሩጫ ለብርቱካን!

ሰሞኑን የኢትዮጵያ የሰብአዊ ደርጅት በወ/ት ብርቱካን ስም ታላቅ ሩጫ **በጀርመን ትዩቢንገን** ከተማ ለማድረግ እየተዘጋጁ መሆናቸውን ሰምተናል። እኛ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የምንገኝ ይህንን ዓላማ በመደገፍ ሁሉም በተለያየ መስኩ በሚችለው እንዲሳተፍ ጥሪያችንን ልናቀርብ እንወዳለን፡፡ ሯጭም ይሁኑ የእግር ተጓዥ ይህንን ጥሩ አጋጣሚ ተጠቅመው ሰውነትዎን አንቀሳቅሰው በዚያውም ይህችን የአገራችህንን ታላቅ ጀግና እንዲያስታውሱ ልባዊ ጥሪያችንን ልናስተላልፍ እንወዳለን፡፡ ይህ ሩጫ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ስም ይዘጋጅ እንጂ በአገራችን በፖለቲካ አመለካከታቸው ብቻ በእስር ቤት የሚማቅቁ ሌሎችንም የሚያካትት ነው፡፡



ለብዙዎቻችን ኩራት የሆነችው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የ35 ዓመት ወጣት እና የልጅ እናት ብቻ ሳትሆን ህግ አክባሪ፣ መሪ፣ ዳኛ፣ እናት እና ቃሏን የምታከብር የእውነት ተምሳሌትም ነች፡፡ ‹‹ቃል››ን ማክበር እጅግ አስቸጋሪ በሆነበት በዚህ ዘመን ‹‹የተናገርኩት ከሚጠፉ የወለድኩት ይጥፉ›› በማለት ፍቅሯን ያልጠገበቻትን ልጇን እና አዛውንት እናቷን በሃዘን በመለየት ለ‹‹ቃሏ›› የቆመች ቆራጥ መሪ ነች፡፡ በዚህ ቃሏ ብቻ የዕድሜ ልክ እስራት በአምባገነኑ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ መሪ ተውስኖባት በጨለማ ክፍል ውስጥ ከታሰረች ይኸው ሁለት ዓመት ሊሆናት ነው፡፡ ህጻን ልጇ ሃሌ በ75 ዓመት አዛውንት የብርቱካን እናት የምታድግ ልጅ ስትሆን በ9 ወሯ ከእናቷ ለሁለት ዓመት ተለይታ እንደገና አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ በሳምንት አንድ ቀን ብቻ እሷና አያትዋ ለተወሰነች ደቂቃ ብርቱካንን ሲጎበኙ ሁለት ዓመት ሊሆናቸው ነው፡፡ ልጆች ያሉን ወይም በቤተሰባችን ውስጥ ህጻናት ያለን በዚህ ሁኔታ ላይ ራሳችንን አስገብተን እስቲ ለጥቂት ደቂቃ እናስበው፡፡ አንድ ቀን ማደር እንችል ይሆን? ብርቱካን ግን ይህንን ላለፉት 600 ቀናት በላይ አሳልፋለች ወደፊትም ትቀጥላለች፡፡

ስለዚህ የብርቱካንን የፖለቲካ አስተሳሰብ የምንጋራ ባንሆንም እንኳን ኢትዮጵያንና ህዝቧን የምንወድ በሙሉ ለሰብዓዊ መብት ስንልና በዚህ መከራ ውስጥ ለወደቁት ህጻን ሐሌና ለአዛውንቷ ወ/ሮ አልማዝ ስንል ለዚህች ወጣት ሴት መፈታት የቀረበውን ጥሪ የምንችል በሩጫው ላይ በመሳተፍ የማንችል ደግሞ አዘጋጆቹን በስልክ ቁጥር 0160-4357232 እና በኢሜይል menschenrecht-ethiopia@hotmail.de በማግኘት የሚፈልጉትን ነገር በመጠየቅ ይህንን የተቀደሰ ዓላማ እንደግፍ፡፡

ብርቱካን ሚደቅሳና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር
አይዳ ኃይሉ
የዓለም አቀፍ ግብረኃይል ኃላፊ
Aida@solidaritymovement.org

